አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

4

ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት

በቴሌግራም

2

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል

"ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው"

إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

"አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡"

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ

የአፍሪካ አካዳሚ

የርቀት ትምህርት

1441 ሒጅሪያ/2020

በመላኢኮች ማመን

በመላኢኮች ማመን ማለት ምን ማለት ነው?

መላኢኮች የተባሉ ፍጡሮች በመኖራቸውና አላህ (ሱ.ወ) ጥራት የተገባውን ጌታ ሊገዙትና ትዕዛዙን ሊተገብሩ የተፈጠሩ ናቸው ብሎ ማመን ነው።

አላህ በቁርአን "(መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው።
በንግግር አይቃወሙትም (ያላለውን አይሉም)፤ እነሱም በትእዛዙ መሰረት ይሰራሉ።) ይላል።

በመላዕክት ማመን ሲባል ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል፡፡

1- መኖራቸውን ማመን፤
2- ስማቸውን ያወቅናቸውን እንደጂብሪል ያሉትን ከነስማቸው ማመን፤
3- ከባህሪያቸው ያወቅነውንና እነሱ የተለዩበትን ግዙፍነታቸውን ይመስል ለይቶ ማወቅ፤
4- ያወቅነውንና እነሱ የተለዩበትን ተግባር ለምሳሌ እንደሞት መላኢካ ያለውን ከነተግባሩ ለይቶ ማመንና ማወቅ ነው፡፡

በመላኢኮች ማመን ስንል ከኑር (ከብርሃን) የተፈጠሩ መሆናቸው እንዲሁም አላህ ያዘዛቸውን የሚተገብሩ መሆናቸው፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፦

(አላህ ባዘዛቸው ነገር ላይ የማያምፁና የታዘዙትን ያለምንም ማቅማማት የሚፈፅሙ መላእክቶች አሉ።)

የመላኢኮች ስራ ምንድነው?

የመላኢኮች አለቃ ጂብሪል አሌይሂ ሰላም ወህይን እንዲያስተላለፍ የተመደበ ሲሆን የርሱም ክብር ከተመደበበት ኃላፊነት ትልቀት የተነሳ ነው፡፡

በመላኢኮች ማመን

በመላእኮች ማመን ብዙ ነገሮችን የሚያካትት በመሆኑ አንድ ሰው በመላእኮች በሚገባው መልኩ እንዲያምን እነዚህን ማወቅ ያስፈልገዋል፡፡

1.እንዳሉ በእርግጠኝነት ማመን

2.እጅግ የበዙና ቁጥራቸውን ከአላህ ሌላ ማንም ሊያውቅ እንደማይችል ማመን፡፡

3.ጌታቸው ዘንድ ከፍተኛ ማዕረግና የላቀ ደረጃ እንዳላቸው ማመን፡፡

4.ማዕረጎቻቸው እንደሚለያዩና አንዱ ከሌላው እንደሚበላለጥ ማመን፡፡

5.እነሱን መወዳጀት የእነሱን አርዓያ መከተል እነሱን ከመጥላት መጠንቀቅ፡፡

6.አንዳንድ ስማቸው ወይም ባህሪያቸው በቁርአንና ሀዲስ በተጠቀሱ መላእኮች በእያንዳንዱ ተናጥል የሆነ ኢማን ማመን፡፡

በመላኢኮች ማመን

በመላኢኮች ማመን ማለት ምን ማለት ነው?

መላኢኮች የተባሉ ፍጡሮች በመኖራቸውና አላህ (ሱ.ወ) ጥራት የተገባውን ጌታ ሊገዙትና ትዕዛዙን ሊተገብሩ የተፈጠሩ ናቸው ብሎ ማመን ነው፡፡

አላህ በቁርአን “(መላእክት) የተከበሩ ባሮች ናቸው፡፡
በንግግር አይቃወሙትም (ያላለውን አይሉም)፤ እነሱም በትእዛዙ መሰረት ይሰራሉ፡፡) ይላል፡፡